ቃ6

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ፍትህ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር የሕ/ም/ማጠ/ዳ/ ፲፩ቃ፲/18

ቀን 06/05/2018 ዓ.ም

ለአብክመ ሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ሀብት ልማት ቢሮ
ባህር ዳር፤

ጉዳዩ፦ የመመሪያ ምዝገባን ይመለከታል

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም እንደተደነገገው ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዲስ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው እንዲሁም አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አዋጁ በወጣ በ1 (አንድ) ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮው በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል።

በዚህ መሰረት የአብክመ ሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ሀብት ልማት ቢሮ በቁጥር ሰ/ሰ/ኮ/786 በቀን 15/03/2018 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ "የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች፣ ባለሙያዎችና የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የዝውውር አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 20/2016" ዓ.ም" ምዝገባ እንዲከናወን መላኩ ይታወሳል።

ስለሆነም ፍትህ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 መሠረት የተላከለትን መመሪያ ሕጋዊነቱን፣ መሰረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮ መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 36/2018 ዓ.ም ሆኖ ስራ ላይ እንዲዉል የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ...3፬..... ገጽ በሀርድና ሶፍት ኮፒ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

'ከሰላምታ ጋር'

ሺፈራው ኃይሌ
የክልል ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ//

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤ (ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት
  ፍትሕ ቢሮ

# የተሻሻለዉ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች፣ ባለሙያዎች እና የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የዝውውር አፈጻጸም መመሪያ

ሰኔ/2016 ዓ.ም

ባህር-ዳር

# መመሪያ ቁጥር 36/2018

## የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች፣ ባለሙያዎችና የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የዝውውር አፈጻጸም መመሪያ

የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች፣ ባለሙያዎች እና የቀበሌ ግብርና ጽህፈት ቤት ሀላፊዎች ለአርሶ አደሩ የግብርና ኤክስቴንሽን የምክር አገልግሎት በመስጠት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲቻል ባለሙያዎችን ማበረታታት ስለሚገባ፣ ከቀበሌ ወደ ቀበሌ የሰራተኞች፣ ባለሙያዎችና የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ሀላፊዎች የዝውውር መመሪያ ተዘጋጅቶ በስራ ላይ ተግባራዊ መደረጉ ጠቀሜታዉ በመረጋገጡና ባለሙያዎች በስራ ቦታቸዉ ተረጋግተዉ እንዲሰሩ ለማስቻል፤

ከጥቅምት 2013 ዓም ጀምሮ በስራ ላይ የነበረው የቀበሌ ሰራተኞች/ባለሙያዎች/ እና የግብርና ጽ/ቤት ሀላፊዎች የዝውውር አፈጻጸም መመሪያ በአተገባበር ላይ የነበሩበትን የግልጽነት ችግርና የሚነሱ አቤቱታዎችን መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ የቀበሌ ግብርና ሰራተኞች/ ባለሙያዎች/ እና የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ሀላፊዎች የስራ ተነሳሽነት ለማሳደግ፣ታታሪና ውጤታማ የሆኑ ሠራተኞች/ ባለሙያዎች/ የጽ/ቤት ኃላፊዎች እንዲበረታቱ ለማድረግ፤

ከዞን ግብርና መምሪያና ከወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች እንዲሁም ከራሳቸው ከቀበሌግብርና ባለሙያዎች የቀረበ ቅሬታ በስራ ላይ የነበረው መመሪያ ለአፈፃፀም የሚያስቸግር በመሆኑ የወጣውን የቀበሌ ግብርና ልማት ባለሙያዎች የዝውውር መመሪያ መከለስ አስፈልጓል።

በመሆኑም የአፈፃፀም ችግሮችን በመለየት የአብክመ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በአዋጅ ቁጥር 253/2010 አንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን የተሻሻለው የቀበሌ ግብርና ሰራተኞች፣ ባለሙያዎች እና የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ሀላፊዎች የዝውውርና ምደባ መመሪያ አዘጋጅቷል።

## ክፍልአንድ

## ጠቅላላ

**አንቀጽ 1 አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች፣ ባለሙያዎችና የቀበሌ ጽህፈት ቤት ኃላፊዎች የዝውውር አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 36/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀጽ 2 ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "ቢሮ" ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮን፣ መሬት ቢሮን፣ ህብረት ስራ ማህበራት ባለስልጣንን እና እንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ኤጀንሲን ያካትታል፡፡
2. "ኮሚሽን" ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ኮሚሽን ነው፡፡
3. "የቀበሌ ግብርና ጽህፈት ቤት" ማለት በቀበሌ ደረጃ የተቋቋመ የግብርና ልማት ስራዎች አገልግሎት መስጫ ተቋም ነው፡፡
4. "የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞችና ባለሙያዎች" ማለት በቀበሌ ተመድበው እያገለገሉ ያሉ የቀበሌ ሰብል ልማትና ጥበቃ፣ የቀበሌ የእንስሳት ሀብት ልማት፣የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ፣ የቀበሌ መስኖ፣ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ባለሙያዎች፣ የቀበሌ እንስሳት እርባታ ባለሙያ፣ የእንስሳት አዳቃይ ቴክኒሽያኖች፣ የቀበሌ ኅብረት ስራ አደራጆች እና የቀበሌ ገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ሠራተኞችና ባለሙያዎችን ያካተተ ነው፡፡
5. "የቀበሌ ግብርና ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ" ማለት በቀበሌው ውስጥ የሚያገለግሉ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞችንና ባለሙያዎችን ቀበሌ ላይ ሆኖ የሚያስተባብር፣ የሚደግፍ፣ የሚከታተልና የሚቆጣጠር ማለት ነው፡፡
6. "የስራ ልምድ" ማለት በመንግስትም ሆነ ህጋዊ ከሆኑ መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ውስጥ በማንኛውም የስራ አይነት በቋሚነት ወይም በኮንትራት የወር ደመወዝ

እየተከፈላቸው በመደበኛ የስራ ሰዓት የመንግስት የስራ ግብር ተከፍሎ የተገኘ አገልግሎት ነው ፡፡

7. "መደበኛ ዝውውር" ማለት የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኛ/ባለሙያ/ ወይም የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ በፍላጎታቸው በአመት አንድ ጊዜ በሞሉት ቅፅ በየደረጃው በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ከሚሰራበት ቀበሌ ወደ ሌላ ቀበሌ፤ ወይም ወደ ሌላ ወረዳ/ዞን ውስጥ በሚገኝ ቀበሌ የሚደረግ የዝውውር ዓይነት ነው፡፡
8. "የክልል ክልል ዝውውር" ማለት ከአማራ ክልል ወደ ሌሎች ክልሎች/ የፌደራል ተቋማት ወይም ከሌሎች ክልሎች/የፌደራል ተቋማት ወደ አማራ ክልል የሚደረግ ዝውውር ነው ፡
9. "የእርስ በእርስ ዝውውር" ማለት ሁለት ሰራተኞች እርስ በእርስ ፈቅደው የሚያደርጉት የዝውውር አይነት ነው ፡፡
10. "ምደባ" ማለት በተሿሚነት ወይም በህዝብ ተመራጭነት ምክንያት ከትዳር በመነጣጠል፣ የህግ ከለላ ለሚያስፈልጋቸው የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኛ/ባለሙያ/ ወይም የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ ምደባ ሲጠየቅ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መመደብ ነው
11. "የደህንነት ስጋት" ማለት በስራ አካባቢ ተረጋግቶ ስራን ለመስራት የማያስችልና በህይወት የመኖር ስጋት ነው ፡፡
12. "የህግ ከለላ የሚያስፈልጋቸው" ማለት የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 699/2003 መሰረት በጠቋሚ ወይም በምስክር ወንጀል ምርመራ፣በወንጀል ክስ ወይም በወንጀል ማጣራት ሒደት መረጃ ወይም ምስክርነት የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ ነው ፡፡
13. "የህክምና ቦርድ ማስረጃ" ማለት በመንግስት ሪፈራል ሆስፒታል ደረጃ በሀኪሞች ሜዲካል ቦርድ ታማሚው ያለበትን የጤና ሁኔታና ምን ሊደረግለት/ሊታገዝ እንደሚገባ የሚገልፅ የህክምና ማስረጃ ነው ፡፡

14. "ተሿሚ" ማለት በየትኛውም የሲቪል ሰርቪስ መዋቅር ላይ በክልሉ ም/ቤት፣ በብሔረሰብ ዞን አስተዳደር ም/ቤቶች ወይም በክልል ርዕሰ መስተዳድር፣ ም/ርዕሰ መስተዳድር፣ በወረዳ፣ በቀበሌ ም/ቤቶች እና የመሾም ስልጣን በተሰጠው አካል በሹመት የሚመደብ

ሰው ማለት ነው፡፡እንዲሁም የመንግስት ሰራተኛ እያሉ በቀጥታ ወደ ልማት ድርጅቶችና ብዙሃን ማህበራትና ሙያ ማህበራት የተሾሙትን ያካትታል፡፡ ሆኖም ግን በሲቪል ሰርቪስ መዋቅር ሳይልፉ በቀጥታ ወደ መንግስት ልማት ድርጅቶችና ብዙሃን ማህበራት የተሾሙትን ለዚህ መመሪያ አተገባበር እንደ ተሿሚ አይቆጠሩም ፡፡

15. "የስራ ቦታ ምድብ ደረጃ" ማለት በአየር ጠባይ ተስማሚ አለመሆን ወይም በመሠረተ ልማት ኋላቀርነት የሚታይበት፣ ከወረዳ ዋና ከተማ ያለው ርቀትና በሌሎችም መስፈርቶች የተሰጠ የቦታ ደረጃ ነው፡፡
16. "የጋብቻ ማስረጃ" ማለት በማዘጋጃ ቤት ወይም በወሳኝ ሁነቶች ምዝገባ ክፍል ወይም በሃይማኖት ተቋም ወይም በባህላዊ ጋብቻ /የአገር ሽማግሌ/የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፡፡
17. "ጊዚያዊ ምደባ" ማለት በተለያዩ የግብርና ሙያ ዘርፎች ግብርና ቢሮ ስር ካሉ ግብርና ኮሌጆች ትምህርቱን አሻሽሎ ሲመለስ፤አዲስ ለሚቀጠሩ ባለሙያዎች ፣ከቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊነት ሲነሳ ከሙያና ከትምህርት ዝግጅት አኳያ ታይቶ በተገኘው ክፍት የስራ መደብ የሚደረግ ጊዚያዊ የስራ ምደባ ነው፡፡
18. "አካል-ጉዳተኛ" ማለት ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም በደረሰበት የአካል፣ የአእምሮ ወይም የስሜት ሕዋሣት ጉዳትን ተከትሎ በሚመጣ የኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ መድሎ ሣቢያ በሥራ ስምሪት የእኩል ዕድል ተጠቃሚ ያልሆነ ሰው ሲሆን አንድ ሰው የአካል ጉዳተኛ ተደርጐ የሚወሰደው ሙሉ በሙሉ አይነ ስውር ወይም ሙሉ በሙሉ መስማት የተሣነው ወይም በተጨማሪ ድጋፍ የሚንቀሣቀስ ወይም በተጨማሪ ድጋፍ ባይንቀሳቀስም በግልጽ በሚታይ ሁኔታ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ አደጋ ምክንያት በአጋጠመው ጉዳት የተነሳ የአንቅስቃሴ ችግር ያለበት ሰው ነው፡
19. "የዝዉዉር የቅድሚያ ዕድል ተጠቃሚ" ማለት የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኛ/ ባለሙያ/ ወይም የግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ በጤና መታወክ ወይም በህይወት የመኖር የደህንነት ስጋት ችግር ሲያጋጥም በመደበኛ ዝዉዉር ወቅት የሚፈፀም ነዉ፣

እንቀጽ3. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በክልሉ ውስጥ ተመደበው በሚሰሩ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች፣ ባለሙያዎችና የግብርና ጽ/ቤት ኃላፊዎች በሙሉ ተፈጻሚ ይሆናል።

አንቀጽ 4. የፆታ አገላለፅ፣

በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀዉ ሁሉ የሴት ፆታን ያካትታል።

## ክፍል ሁለት

## የዝውውር አፈጻጸም

አንቀፅ 5. የዝውውር አይነቶች፣

1. መደበኛ ዝውውር
2. የእርስ በርስ ዝውውር
3. በዝውውር ምደባ
4. የክልል ክልል ዝውውር

አንቀጽ 6.ዝውውሩ የሚፈፀምባቸው የአስተዳደር እርከኖች /ደረጃዎች/

ሀ. ከቀበሌ ወደ ቀበሌ

ለ. ከወረዳ ወደ ወረዳ

ሐ. ከዞን ወደ ዞን

መ. ከክልል ክልል ናቸው። ሆኖም ከወረዳ ወደ ወረዳ፣ከዞን ወደ ዞን እና ከክልል ክልል ዝዉዉር ሲባል ወደ ግብርና ቢሮ/መምሪያ/ጽ/ቤት ሳይሆን በሚዛወርበት የአስተዳደር ዕርከን በቀበሌ ደረጃ ምደባዉ የሚፈፀም ይሆናል።

አንቀፅ 7. ዝውውር ከመፈፀሙ በፊት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤

1. የተፈቀደ ክፍት የሥራ መደብ በሙያ አይነትና ብዛት በመለየት እና በጀት መኖሩን ማረጋገጥ
2. በተለያዩ ምክንያት በጊዚያዊነት የተመደቡ የቀበሌ ግብርና ልማት ባለሙያዎችወይም ጽ/ቤት ሃላፊዎች የዝውውር ፎርም እንዲሞሉ በማድረግ ተመድው የነበሩበት የስራ መደብ ለመደበኛ ዝውውር ክፍት መደረጉን ማረጋገጥ

3. በየዓመቱ የሚደረገው ዝውውር ክፍት በሆኑ ቀበሌዎች፣ ፍላጐትን መሠረት ያደረገና በውድድር የሚፈጸም ሲሆን ዝውውር ፈላጊው ከቀበሌ፣ወረዳና ዞን ወደ ሌላ ቀበሌ፣ ወረዳ፣ዞን ለመዛወር በተመደበበት ቀበሌ ሁለት ዓመት ማገልገል ይጠበቅበታል፡፡
4. ያላግባብ የሰው ኃይል ስብስብ የማይፈጥር መሆኑን ማረጋገጥ ፤
5. የዝውውር መሙያ ፎርም ለሁሉም ዝውውር ፈላጊዎች እኩል መድረሱንና የመደበኛ ዝውውር ማስታወቂያ መለጠፉን ማረጋገጥ
6. ለመደበኛ ዝውውር የተጠየቀው መረጃ በአግባቡ እና በጥንቃቄ ተሞልቶ በወቅቱ በየደረጃው ለሚገኙ አስፈጻሚ አካላት መድረስ ይኖርበታል፡፡
7. ለመዛወር የዝውውር ፎርም በጊዜ ገደቡ ውስጥ መሙላት ግዴታ ነው፡፡
8. ዝውውር ፈላጊዎች ፍላጎትን መሰረት በማድረግ በሚዛወርበት የአስተዳደር ዕርከኑ 3 ቦታዎችን በቅደም ተከተል መሙላት ይችላሉ፡፡ ሆኖም መረጃው ስርዝ ድልዝ ካለው ተቀባይነት አያገኝም፡፡
9. በወረዳው ካሉት የቀበሌ ቁጥር በላይ በተመሳሳይ ሙያ ትርፍ ባለሙያ በሚኖርበት ጊዜ የዝውውር ፎርም ከመሞላቱ በፊት ባለው ትርፍ ባለሙያ ቁጥር ልክ በየሙያ ዘርፉ ተደራቢ ባለሙያ የሚመደብባቸው ቀበሌዎች ተዘርዝረው መለጠፍ አለባቸው፡፡

አንቀፅ 8. ዝውውር ፈላጊው የዝውውር ፎርም አሞላል

1. በወረዳ ውስጥ ከቀበሌ ቀበሌ ዝዉዉር ጠያቂዉ መዛወር የሚፈልገዉን ቀበሌ እስከ 3 በቅደም ተከተል መሙላት ይችላል፡፡
2. ዝዉዉር ጠያቂዉ በዞኑ ውስጥ ከወረዳ ወረዳ መዛወር የሚፈልገውን እስከ 3 ወረዳዎች በቅደም ተከተል በመምረጥ በዝዉዉር ፎርሙ ላይ መሙላት ይችላል፡፡
3. ዝዉዉር ጠያቂዉ ከዞን ዞን መዛወር የሚፈልገውን እስከ 3 ዞኖች ከነወረዳቸው በቅደም ተከተል በመምረጥ በዝዉዉር ፎርሙ ላይ መሙላት ይችላል፡፡ ሆኖም ከዞን ዞን በሚደረገው ዝውውር በደረጃ ከሞላቸው 3 ወረዳዎች ክፍት ባይኖር በዞኑ ውስጥ ባሉ ማንኛውም ወረዳዎች ተዛውሮ ለመስራት ፈቃደኛ መሆኑን ከዝውውር ፎርሙ አብሮ ማመላከት አለበት፡፡
4. በየትኛውም ደረጃ ተሞልቶ የተላከ የዝውውር ጥያቄ የሚያገለግለው ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

እንቀጽ 9.የዝውውር ማወዳደሪያ መስፈርቶች

ሀ. የስራ አፈጻጸም ውጤት ............................ 40%

ዝውውሩ ከመታየቱ በፊት ባሉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት የመጨረሻ የዕቅድ አፈጻጸም መገምገሚያ ወቅት የተሞላ የ4 ተከታታይ ጊዜ የስራ አፈጻጸም ምዘና አማካይ ውጤት 40% የሚያዝ ሆኖ /የተገኘው ውጤት በ0.4 እየተባዛ ይያዛል። ሆኖም በስራ አፈፃፀም አያያዝ መመሪያ መሰረት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ውጤት ያልተሞላላቸው ዝውውር ፈላጊዎች ቀደም ሲል ተሞልቶ ማህደራቸው ላይ በተያያዘው የቅርብ ተከታታይ የሁለት ጊዜ ስራ አፈጻጸም ውጤት መሰረት እንዲወዳደሩ ይደረጋል፡፡ ሆኖም የቅርብ ተከታታይ የሁለት ጊዜ ስራ አፈጻጸም ውጤት የሌላቸው የዝውውር ተጠቃሚ አይሆኑም ፡፡

ለ. የአገልግሎት ዘመን ................................45%

ለአገልግሎት 45% ነጥብ የሚይዝ ሆኖ 40 ዓመትና በላይ አገልግሎት ያለው 45% የሚያገኝ ሲሆን ከ40 ዓመት በታች አገልግሎት ያለው ዝውውር ፈላጊ አገልግሎቱ በ1.125 እየተባዛ የሚያዝ ይሆናል። ይሁን እንጅ ለኑሮ አስቸጋሪ በሆኑ ቦታዎች እየሰሩ ለሚገኙ ዝውውር ፈላጊዎች ለቦታው የተሰጠው አገልግሎት በተፈቀደው መሰረት የሚታሰብ ይሆናል። ሆኖም ግን ለኑሮ አስቸጋሪ በሚያደርጉ ቦታዎች የተገኘ ልምድ የሚያገለግለው በቦታው ላይ እስካሉ ድረስ ብቻ ነው፡

ሐ. ለስራ ቦታ ............................................ 5%

ለሚሰሩበት ቦታ ለኑሮ ተስማሚነት ደረጃ 5% የሚይዝ ሆኖ የስራ ቦታዎች በ4 ምድብ ወይም ደረጃ በመክፈል ማለትም በከፍተኛ ደረጃ ለኑሮ አስቸጋሪ፣ በመካከለኛ ደረጃ ለኑሮ አስቸጋሪ፣ በዝቅተኛ ደረጃ ለኑሮ አስቸጋሪ በሚል በየደረጃው ያለው ቀበሌው ከወረዳው ርዕሰ ከተማ ያለው ርቀት የገጠር መሰረተ ልማት መስፋፋት እና የአየር ንብረት ሁኔታ አስቸጋሪነት ግምት ውስጥ በማስገባት ደረጃ በማዘጋጀት ለወረዳ /ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት በማቅረብ ደረጃው እየተወሰነ ከዚህ በታች በተመላከተው ደረጃ ነጥብ እየተሰጠ ከቀበሌ ቀበሌ ዝውውር ይሰራል።

- በከፍተኛ ደረጃ ለኑሮ አስቸጋሪ ናቸው ተብለው ለተፈረጁ ቀበሌዎች 5 %
- በመካከለኛ ደረጃ ለኑሮ አስቸጋሪ ናቸው ተብለው ለተፈረጁ ቀበሌዎች 3 %
- በዝቅተኛ ደረጃ ለኑሮ አስቸጋሪ ናቸው ተብለው ለተፈረጁ ቀበሌዎች 1 %
- ለኑሮ ምቹ የሆነ ናቸው ተብለው ለተፈረጁ ቀበሌዎች 0% ሆኖ ከዞን ዞን ፣ ከወረዳ /ከአስተዳደር ወደ ሌላ ወረዳ /ከአስተዳደር ተዛውረው የሚመጡ የቀበሌ ግብርናሰራተኞች/ባለሙያዎች/ ወይም ጽ/ቤት ሀላፊዎች ይሰሩበት የነበረው ቀበሌ የቦታ ምድብ ደረጃ በዝውውር ፎርሙ ተሞልቶ መላክ አለበት ፡፡ ተሞልቶ ያልተላከለት ቢኖር ለኑሮ ምቹ በሆነ ቦታ ይሰራ እንደነበረ ተደርጎ ይሰላል ፡፡

መ. የማህደር ጥራት ..................... 5% የሚይዝ ሆኖ አፈፃፀሙ እንደሚከተለው ይሆናል፡ ፡

| ተ.ቁ | የተወሰደው የዲስፕሊን እርምጃ | የሚቀነስ ነጥብ | የሚሰጥ ነጥብ |
|---|---|---|---|
| 1 | እስከ 2 ዓመት ለሚደርስ ጊዜ ከደረጃና ደመወዝ ዝቅ ማድረግ | 5 | 0 |
| 2 | እስከ ሦስት ወር ደመወዝ የሚደርስ የደመወዝ ቅጣት | 4 | 1 |
| 3 | እስከ አስራ አምስት ቀን የሚደርስ የደመወዝ ቅጣት | 3 | 2 |
| 4 | የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ቅጣት | 2 | 3 |
| 5 | የቃል ማስጠንቀቂያ በጽሑፍ ከተቀመጠ | 1 | 4 |
| 6 | ምንም የቅጣት ሪከርድ የሌለበት | 0 | 5 |

ሠ. የጋብቻ ሁኔታ ......................................... 5%

ህጋዊ የጋብቻ ማስረጃ የሚያቀርቡ ባለትዳሮች ዝውውር የሚጠይቁት አንድ ላይ እንዲኖሩ ለማድረግ ብቻ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ የጋብቻ ማስረጃው ከዝውውር ፈላጊ ማህደር ከተያዘ 6 ወር ሆኖት ተቀባይነት ሲያገኝ ለትዳር 5 ነጥብ ይሰጣል፡፡ ይህም ሆኖ የትዳር አጋሩ የመንግስት ሰራተኛ በመሆንና ባለመሆን ልዩነት ሳይደረግ ተግባራዊ ይደረጋል ፡፡

ረ. ለሴት ተወዳዳሪዎች ለጾታ 3 ነጥብ ይሰጣል፡፡ ይህም ሆኖ ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል ውጤት ካመጡ ቅድሚያ ለሴት ይሰጣል፡፡

ሰ. ለአካል ጉዳተኞች ለሴት 4 ለወንድ አካል ጉዳተኛ 3 ነጥብ ይሠጣል፣ ከአንድ በላይ የልዩ ድጋፍ ተጠቃሚ የሚሆን ዝውውር ፈላጊ የተሻለውን ነጥብ ይወስዳል፤ተወዳደሪዎች ያመጡት ውጤት እኩል ከሆነ ቅድሚያ ለሴት አካል ጉዳተኛ ይሰጣል ይህ ከሌለ ለወንድ አካል ጉዳተኛ ይሰጣል።

ሸ. ከቀበሌ ቀበሌ ከሚካሄደው ዝውውር ውጭ ለወረዳ ወረዳ እና ለዞን ዞን ለሚካሄደው ዝውውር ከ95% በሚገኘው ውጤት መሰረት ዝውውሩ የሚፈፀም ይሆናል ።

አንቀጽ 10. መደበኛ ዝውውር

ሀ. ከዞን ዞን የተዛወሩ ዝውውር ፈላጊ በተዛወረበት ዞን ከወረዳ ወረዳ ዝዉዉር ከሞሉ የቀበሌ ዝውውር ፈላጊዎች ጋር እኩል የመወዳደር መብት ያላቸው ሲሆን ተወዳድረው በተመደቡበት ቦታ የመስራት ግዴታ አለባቸው።

ለ. ከወረዳ ወረዳ የተዛወሩ ዝውውር ፈላጊዎች በተዛወሩበት ወረዳ ከቀበሌ ወደ ሌላ ቀበሌ ዝዉዉር ከሞሉ ዝውውር ፈላጊዎች ጋር እኩል የመወዳደር መብት ያላቸው ሲሆን ተወዳድረው በተመደቡበት ቦታ የመስራት ግዴታ አለባቸው።

ሐ. ህጋዊ የጋብቻ ማስረጃ የሚያቀርቡት ባለትዳሮች ዝውውር የሚጠይቁት አንድ ላይ ለመኖር ብቻ ነው ። ባልና ሚስት የዝውውር ጥያቄ ፎርም ሲሞሉ የጋብቻ ማስረጃ ከሁለቱም ሰራተኞች ወይም ዝውውር ጠያቂ ባለሙያ የግል ማህደር ላይ ከሰድስት ወር በፊት የተያያዘ መሆን አለበት። በአንድ ላይ የሚኖሩ ባለትዳሮች ተነጣጥለው መዛወር የማይፈልጉ ከሆነ ይህው ጉዳይ በማሳሰቢያ ይገለፅ፣ ከሁለት አንዱ በዝውውሩ የማያሸንፉ ከሆነ በውድድሩ ያሸነፈው ተወዳዳሪ ተሰርዞ ቀጥለው ያሉ ሌሎች ተወዳዳዎች እንዲገቡ ይደረጋል። በአንድ ላይ የሚኖሩ ባለትዳሮች ተነጣጥለው መዛወር የሚፈልጉ ከሆነ በተናጠል ባለቸው አገልግሎት ብቻ የሚወዳደሩ ሆኖ ለጋብቻ የሚሰጠው ልዩ ድጋፍ ተጠቃሚ አይሆኑም ፡

መ. ባል ወይም ሚስት የመንግስት ሰራተኛ ቢሆኑም ባይሆኑም የጋብቻ ማስረጃዉ በአንቀጽ 9 “መ” መሰረት ከፋይላቸው ጋር የተያያዘና የመንግስት ሰራተኛ ከሆኑ ከሚሰሩበት መ/ቤት የመንግስት ሰራተኛ ካልሆኑ ደግሞ ከሚኖሩበት ቀበሌ የኗሪነት ማረጋገጫ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። ይህም ወደ አወዳዳሪው ተቋም መላክ አለበት።

ሡ. ባል ወደ ሚስት ወይም ሚስት ወደ ባል ለመዛወር ሲጠይቁ ለተወዳዳሪው የባልናሚስትየሁለቱ አገልግሎት ተደምሮ ሲካፈል በሚገኘው አማካይ የአገልግሎት ውጤት ተይዞ ይወዳደራሉ፡፡ሆኖም የባል ወይም የሚስት በተናጠል ያላቸው አገልግሎት ከአማካይ አገልግሎቱ የሚበልጥ ከሆነ ይህው ተይዞላቸው አብሮ ለመኖር ብቻ ማወዳደር ይቻላል፡፡

ረ. ባል ወይም ሚስት በዝውውር መጠየቂያ ቅጽ ላይ መረጃውን በትክክል መሙላት ይገባቸዋል፡፡ ሳይሞሉ ቀርተው ዝውውሩ በተናጠል ከታየ በኋላ የሚቀርብ የዝውውር ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

ሰ. ለቀበሌዎች ያለዉን የሥራ አመችነት፣ የገጠር መሠረተ ልማት መስፋፋት፣ የአየር ንብረት ሁኔታንና የስራ ቦታ ቅርበት መሰረት በማድረግ ለስራ ቦታ የተሰጠውን ደረጃ ሁሉም ዝውውር ፈላጊዎች እንዲያወቁት እና በተመደቡበት ቀበሌ በመስራታቸው የሚሰጣቸው ነጥብ ስንት እንደሆነ በቅድሚያ ማወቃቸውን የማረጋገጥ ስራ ይሰራል፡፡

ሸ. አንድ የቀበሌ ግብርና ሰራተኛ/ ባለሙያ ወይም የግብርና ጽ/ቤት ሃላፊ ካለበት ቀበሌ መዛወር ካልፈለገ ይህንኑ ሀሳቡን ዝውውሩ ከመሰራቱ በፊት በጽሑፍ ማመልከቻ ለቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ማሳወቅ አለበት፡፡

ቀ. የቀበሌ ግብርና ሰራተኞች/ ባለሙያዎች/ ወይም ጽ/ቤት ሀላፊዎች ዝውውር ከተጠናቀቀ በኋላ እስከ 2 ወር ባለው ጊዜ በተለያዩ ምክንያት ቀበሌዎች ክፍት ሲሆኑ ዝውውር ፈላጊዎች ፍቃደኝነት እየተረጋገጠ መደበኛ ዝውውሩ በተሰራበት ውጤት ቅደም ተከተል መሰረት ማዛወርና ማሸጋሸግ ይቻላል፡፡

አንቀጽ 11. የእርስ በእርስ ዝውውር፤

1. የእርስ በእርስ ዝውውር ተመሳሳይ የካርየር ደረጃ፣ተመሳሳይ ሙያና ደመወዝ እንዲሁም ተመሳሳይ የስራ ቦታ ምድብ ደረጃ ያላቸው ሁለት ሰራተኞች እርስ በእርስ ዝውውር ማካሄድ ይችላሉ ፡፡ ሆኖም ደረጃቸውና ሙያቸው ተመሣሣይ ሆኖ ሦስት እርከን የደመወዝ ልዩነት ቢኖርም ላኪና ተቀባይ መስሪያ ቤቶች ከተስማሙ ዝውውሩን ማከናወን ይቻላል፡፡

2. የእርስ በእርስ ዝውውሩ በአንድ ወረዳ ውስጥ በተለያዩ ቀበሌዎች በሚሰሩ ባለሙያዎች ወይም ጽ/ቤት ሃላፊዎች መካከል ከሆነ ሁለቱም የስምምነት ደብዳቢያቸውን በወረዳ ደረጃ ለሚሰሩበት ጽ/ቤታቸው አቅርበው ይሁንታውን ለወረዳው ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት ሲያሳውቅ ዝውውሩም በወረዳው ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት ይፈጸማል፡፡
3. የእርስ በእርስ ዝውውሩ በአንድ ዞን ውስጥ በተለያዩ ወረዳዎች በሚሰሩ ባለሙያዎች መካከል ከሆነ ሁለቱም ከየወረዳቸው በወረዳ ደረጃ ከሚሰሩበት ጽ/ቤታቸው ያመጡትን የስምምነት ደብዳቢያቸውን በዞኑ ለሚሰሩበት መምሪያቸው አቅርበው ይሁንታውን ለዞኑ ሲቪል ሰርቪስ ሲያሳውቅ ፣ ዝውውሩም በዞኑ ሲቪል ሰርቪስ መምሪያ በኩል ይፈጸማል፡፡
4. የእርስ በእርስ ዝውውሩ በተለያዩ ዞኖች መካከል ከሆነ ሁለቱም ከየወረዳቸው ከሚሰሩበት ጽ/ቤታቸውያመጡትን የስምምነት ደብዳቤ ለየዞናቸው ሚሰሩበት መምሪያአቅርበው ተጨማሪ የድጋፍ ደብዳቤ በዞኑ አማካኝነት በክልሉ ለሚሰሩበት ቢሯቸው ሲቀርብ፤ በቢሮው አማካኝነት ዝውውሩ ይፈጸማል፡፡
5. የእርስ በእርስ ዝውውሩ በአማራ ክልልና በሌላ ክልል ባለሙያዎች መካከል ከሆነ ዝውውር ጠያቂው ካለበት ተቋም ስምምነት አስፅፎ በክልል ለሚሰራበት ቢሮ ያቀርባል፤ የክልሉ የሚሰራበት ቢሮም በዝውውሩ ካመነበት ለሌላኛው ክልል የትብብር ደብዳቤ ይፅፋል፡፡ ስምምነት ከተገኘ በቢሮው አማካኝነት እንዲዛወሩ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ዝውውሩ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡ በዚህ ወቅት ካልተጠናቀቀ ዝውውሩ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
6. የእርስ በእርስ የዝውውር ተጠቃሚ ለመሆን ቢያንስ በተመደበበት ቀበሌ ሁለት አመት ያገለገለ፣ጦረታ ለመውጣት 3 ዓመትና በላይ የቀረው መሆን አለበት ፡፡
7. የእርስ በእርስ ዝውውር ማድረግ የሚፈልጉ የመደበኛ ዝውውር ጊዜ ሳይጠብቅ ዝውውሩ ሊፈቀድላቸው ይችላል፡፡
8. የዝውውሩ ሁኔታ ከወረዳ ወደ ወረዳ ወይም ከዞን ወደ ሌላ ዞን ከሆነ በሁለቱ ወረዳዎች የቀበሌ ግብርና ልማት ባለሙያዎች ወይም የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ሃላፊዎች የሚሰሩበት ጽ/ቤቶች ስምምነታቸውን ሲገልፁ በሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤቶች ወይም ሁለቱ ዞኖች የቀበሌ ግብርና ልማት ባለሙያዎች ወይም የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ሃላፊዎች የሚሰሩበት መምሪያዎች ስምምነታቸውን ሲገልፁ በሲቪል ሰርቪስ መምሪያ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

አንቀጽ 12. በመደበኛ ዝውውር ወቅት የቅድሚያ ዕድል ተጠቃሚዎች

1. ከመንግስት ሪፈራል /ስፔሻላይዝድ/ ሆስፒታሎች በቀረበ የህክምና ቦርድ ማስረጃ የሚያቀርቡ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ ባለሙያዎች ወይም የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ሃላፊዎች የሚያቀርቡት የህክምና ማስረጃ ከህክምና ማስረጃ አቀራረብ መመሪያ መሰረት ያደረገና በትክክለኛ የህክምና ማስረጃ ስለመሆኑ በሚሰሩበት የአስተዳደር ዕርከን እናት መ/ቤታቸው አማካኝነት እየተረጋገጠ የሚቀርብ ሆኖ የህክምና ማስረጃው ሠራተኛው በበሽታው ምክንያት አሁን በሚሰራበት ቦታ ላይ መስራት የማይችልበት ሁኔታና መሰል ጉዳዮችን በዝርዝር የሚገልጽ ሆኖ የህክምና ማስረጃው ከተሰጠ አንድ ዓመት ያልበለጠው /የታደሰ/ ሆኖ ሲቀርብ በየደረጃው ያለው እናት መ/ቤታቸው ችግራቸው ወደሚፈታበት የስራ ቦታ ምደባ እንዲሰጣቸው ያደርጋል፡፡ ችግራቸው ያልተፈታለቸው ባለሙያዎች ግን በመደበኛ ዝውውር በውድድር፤-

ሀ. በጤና ችግር ምክንያት ከመንግሥት ሪፈራል/ ስፔሻላይዝድ/ ሆስፒታል በሀኪሞች ቦርድ በተረጋገጠ ማስረጃ የኩላሊት እጥበት የሚደረግላቸው ህሙማን፣የካንሰር ወይም የልብ ህሙማን ስለመሆናቸው ማረጋገጫ የሚያቀርቡ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ ባለሙያዎች ወይም የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ሃላፊዎች ከማንኛውም ዝውውር ፈላጊ በፊት ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡

ለ. ከላይ በአንቀጽ 12 በፊደል ተ.ቁ 1"ሀ" ከተገለፁት ውስጥ ለህመምተኛ አካል ጉዳተኛ ባለትዳር ቅድሚያ ይሰጣል ከአንድ በላይ ከሆኑ በእጣ ይለያሉ፤ለህመምተኛ አካል ጉዳተኛ ባለትዳር ከሌሉ ለህመምተኛ ባለትዳሮች ቅድሚያ ይሰጣል ከአንድ በላይ ከሆኑ በእጣ ይለያሉ፣ህመምተኛ ባለትዳር ከሌሉ ለህመምተኛ አካል ጉዳተኛ ቅድሚያ ይሰጣል ከአንድ በላይ ከሆኑ በእጣ ይለያሉ ፡፡ ከአካል ጉዳተኛ ባለትዳሮች ወይም ከባለ ትዳሮች ወይም ከአካል ጉዳተኞች መካከል የተለያየ ጾታ ያላቸው ከሆነ ለሴት ተወዳዳሪ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

ሐ. ከላይ በአንቀጽ 12 ፊደል ተ.ቁ 1"ሀ" የተገለፁት ከተስተናገዱ በኂላ ወይም በሌሉበት ሁኔታ በሌሎች በሽታዎች ምክንያት በጤና ችግር ከመንግሥት ሪፈራል/ ስፔሻላይዝድ/ ሆስፒታል በሀኪሞች ቦርድ በተረጋገጠ ህሙማን ስለመሆናቸው ማረጋገጫ የሚያቀርቡ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ ባለሙያዎችወይም የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ሃላፊ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል ፡፡

ይህም ሆኖ ከዝውውር ፈላጊዎች መካከል አካል ጉዳተኛ ባለትዳር ካለ ቅድሚያ ይሰጣል ከአንድ በላይ ከሆኑ በእጣ ይለያሉ። አካል ጉዳተኛ ባለትዳር ከሌሉ ለህመምተኛ ባለትዳር ቅድሚያ ይሰጣል ከአንድ በላይ ከሆኑ በእጣ ይለያሉ። ህመምተኛ ባለትዳር ከሌሉ ለአካል ጉዳተኛ ቅድሚያ ይሰጣል ከአንድ በላይ ከሆኑ በእጣ ይለያሉ ። ከአካል ጉዳተኛ ባለትዳሮች ወይም ከባለትዳሮች ወይም ከአካል ጉዳተኞች መካከል የተለያየ ጾታ ያላቸው ከሆነ ለሴት ተወዳዳሪ ቅድሚያ ይሰጣል።

መ. ከላይ በአንቀጽ 12 ተ.ቁ 1"ሀ" ና "ለ" የተገለፀው ቢኖርም ሊዛወሩ የሚችሉበት ተመጣጣኝ የሥራ መደብ ባለመገኘቱ ለጊዜው ከተሰጣቸው የህክምና ቦርድ ማስረጃ አንፃር ችግራቸው ያልተቀረፈላቸው ባለሙያዎች ወይም ጽ/ቤት ሃላፊዎች የተሰጣቸው የህክምና ማስረጃ የታደሰና ዘላቂነት ያለው ከሆነ ለአንድ ጊዜ ብቻ ተጠቅማችሁበታል በሚል ቀጣይ ዝውውር በሚፈፀምበት ጊዜ ሊታገዱ አይገባም።

ሠ. ከላይ በአንቀጽ 12 ተ.ቁ 1"ሀ" ና "ለ" የተገለጹት ዝውውር ጠያቂዎች በሌሉበት ሁኔታ ለአካል ጉዳተኞች ቅድሚያ ይሰጣል።

2. ከላይ በአንቀጽ 12 ተ.ቁ 1"ሀ"፣"ለ"፣ "መ"ና "ሠ" የተገለጹት ዝውውር ጠያቂዎች በሌሉበት ሁኔታ በህይወት ለመኖር የደህንነት ስጋት ወይም የማህበራዊ ችግር የሚያጋጥማቸው ሰራተኞች በሚሰሩበት ቦታ ዋና አስተዳደሪ ለግለሰቡ ከቦታው ካልተነሳ ለህይወቱ አስጊ የሆነና ልንከላከልለት የማንችል መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ ሲሰጥ እና በየደረጃው ከሚገኝ ፖሊስ እና ፍትህ ተቋም የመዝገብ ቁጥሩና መዝገቡ የተከፈተበት ጉዳይ በዝርዝር የሚያሳይ ማስረጃ እንዲሁም የዝምድናው ዓይነት የሚገልፅ ማስረጃ ከፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ማቅረብ ያለበት ሆኖ የዝውውሩ ተጠቃሚ ለመሆን የዝምድናው ደረጀ ልጅ፣ወላጅ ፣ወንድም ፣ እህት እና የወላጅ ወንድምና እህት ብቻ ከሆነ እና በየደረጃው ያለው ሲቪል ሰርቪስ ተቋም የተሰጠው ማስረጃ በትክክለኛ ችግሩ የገጠመው መሆኑን በማረጋገጠ ማስረጃ ሲያቀርቡ በመደበኛ ዝውውር ወቅት የቅድሚያ ዕድል ተጠቃሚዎች ይሆናሉ። ሆኖም ዝውውሩ የሚከናወነው የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ ባለሙያዎች ወይም የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ሃላፊዎች ሲሰራ ከነበረበት ቀበሌ ጋር ተመሳሳይ በሆነ የቦታ ምድብ ደረጃ መሰረት ዝውውሩ ተፈጻሚ ይሆናል።

3. በመደበኛ ዝውውር ወቅት የቅድሚያ ዕድል ተጠቃሚ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ ባለሙያዎች ወይም የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ሃላፊዎች ለአንድ የስራ መደብ ከአንድ በላይ ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡበት ጊዜ የተለያየ ጾታ ያላቸው ከሆነ ለሴት ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ ተመሳሳይ ጾታ ካላቸው በዕጣ ይለያሉ ፡

አንቀጽ13. የዝውውር ምደባ ተጠቃሚዎች

1. የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 699/2003 በተገለፀው መሰረት የህግ ከለላ የሚያስፈልጋቸው የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ ባለሙያዎችወይም የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ሃላፊዎች ከፌደራል ፍትህ ሚንስቴር ሚንስትር/ ደኤታ ወይም ከክልል ፍትህ ቢሮ በኃላፊ/ም/ኃላፊ የተፈረመ ሆኖ የመዝገብ ቁጥሩና መዝገቡ የተከፈተበት ጉዳይ በዝርዝር የሚያሳይ የተጣራና የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉየቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ ባለሙያዎችወይም የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ሃላፊዎች በአንድ ወረዳ ውስጥ ከሚሰራበት ቀበሌ ወደ ሌላ ቀበሌ በወረዳ ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት ፣በአንድ ዞን ከሚሰራበት ወረዳ/ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ ወደ ሌላ ወረዳ/ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ እንዲሁም ከሚሰራበት ከተማ አስተዳደር ቀበሌ ወደ ሌላ ከተማ አስተዳደር/ ወረዳ ቀበሌ በዞን ሲቪል ሰርቪስ መምሪያ በኩል፣ ከአንድ ዞን/ሬጆፖሊታን ከተማ ቀበሌ ወደ ሌላ ዞን/ሬጆፖሊታን ከተማ ቀበሌ የሚደረግ ምደባ ግን በክልሉ በሚሰራበት ቢሮ በኩል በጀት ያለው ክፍት የስራ መደብ እስከተገኘ ድረስ የያዘውን ደመወዝና ደረጃ እንደያዘ በተመሳሳይ የስራ ደረጃ ተመድበው እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ ምደባ የሚካሄደው በተመሳሳይ ባለበት የአስተዳደር እርከን የሚፈፀም ይሆናል ፡፡

2. ከቀበሌ ባለሙያነት ውጭ በየአስተዳደር ዕርከኑ በሚገኙ የስራ መደብ ላይ የሚመደቡ የተሿሚዎች የትዳር አጋር በማንኛውም ጊዜ በሙያቸው በጀት ያለው ክፍት የስራ መደብ እስካለ ድረስ የጋብቻ ማስረጃው በማህደራቸው ከተያያዘ 6 ወርና በላይ መሆኑን በማረጋገጥና ለሚመደቡበት የስራ መደብ ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታውን ማሟላታቸው እየተረጋገጠ በምልመላ መረጣ አቻ ማዛወሪያ ደረጃ መሰረት ተሿሚዎች በሚሰሩበት የስራ ቦታ ተመድበው እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ግን በቀበሌ ባለሙያነት ወይም ጽ/ቤት ሃላፊዎች የሚዛወር ከሆነ የያዙትን ደመወዝና ደረጃ እንደያዙ የትዳር አጋራቸው ወደ ሚሰሩበት የስራ ቦታ በሚገኝ ቀበሌ ተዛውሮ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡

3. የሙያ ማሻሻያ ትምህርታቸውን አጠናቀው የሚመለሱ ባለሙያዎች ቢቻል በመጡበት ቀበሌ ባሻሻሉት ሙያ ክፍት የሥራ መደብ ካለ ይመደባሉ፡፡ ሆኖም ግን በመጡበት ቀበሌ ክፍት ስራ መደብ ከሌለ በሌሎች ቀበሌዎች ባሻሻሉት ሙያ ክፍት የሥራ መደብ በጊዚያዊ ምደባ ይሰጣል፡፡ ሆኖም በተመሳሳይ ሙያ ምደባ የሚሰጣቸው ባለሙያዎች ከአንድ በላይ ከሆኑ የአገልግሎት ዘመናቸው መሰረት በማድረግ በጊዚያዊ ምደባ የሚሰጥ ይሆናል ፡፡

አንቀፅ 14. የክልል ክልል ዝዉዉር

1. ከሌላ ክልል ወደ አማራ ክልል ባሉ የገጠር ቀበሌዎች ተዛዉረዉ መስራት የሚፈልጉ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ባለሙያዎች/ ወይም ጽ/ቤት ሀላፊዎች የዝዉዉር ጥያቄዉን የሚያቀርቡት ለሚቀበላቸዉ በወረዳ ለሚሰሩበት ጽ/ቤት ሆኖ ለመቀበል ፈቃደኛ ከሆነም ለተቀባይ ወረዳ ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት በፅሁፍ በማሳወቅ ዝዉዉሩ እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡ ይሁን እንጂ ዝዉዉር ጠያቂዉ ለሚዛወርበት የስራ መደብ ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታዉን የሚያሟላ ሆኖ የሚከፈለዉ ደመወዝና የስራ ደረጃ ከነበረበት የስራ ደረጃና ደመወዝ ተመሳሳይ መሆን ያለበት ሲሆን የዲስፕሊን ክስ የሌለበት መሆን አለበት፡፡
2. ከአማራ ክልል ወደ ሌላ ክልል ተዛዉረዉ ለመሄድ የሚፈልጉ የቀበሌ ግብርና ሰራተኞች/ባለሙያዎች/ ወይም ጽ/ቤት ሀላፊዎች አሰሪ መስሪያ ቤታቸዉ በዝዉዉሩ የሚስማማ ከሆነ ተዛዉረዉ ወደሚሄዱበት ክልል በወረዳ ሲቪል ሰርቪስ በኩል መሸኛ በፅሁፍ እንዲሰጣቸዉ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለ ምድብና ነጥብ አሰጣጥ

አንቀጽ15. <u>የወረዳዎች አመዳደብና ነጥብ አሰጣጥ</u>

1. ከዞን ዞንም ሆነ ከወረዳ ወረዳ ለሚደረገው ዝውውር የሚያገለግል የስራ ቦታ ምድብ ደረጃ

   ሀ. <u>ምድብ አንድ</u>

   የክልሉን ርእሰ ከተማ ባህርዳርን ጨምሮ ሌሎች የዞን ከተሞች

   ለ. <u>ምድብ ሁለት</u>

የፕንዳ ውኃ እና የዋግህምራ ዞን ርእሰ ከተማ ጨምሮ ከዞን ከተሞች ውጭ የሆኑ ሌሎች ወረዳዎች

ሐ. ምድብ ሶስት

በረኸት፣ ጃን አሞራ፣ መሃል ሳይንት፣ አርጎባ፣ ዳውንት፣ ፣ ዳዋ ሃርዌ፣ ሚዳ ወረሞ፣ ቀወት ፣ ጅሌ ጥሙጋ፣

መ. ምድብ አራት

በየዳ፣ ጠለምት፣ ዳህና ፣ ግሸራቤል

ሠ. ምድብ አምስት

ቋራ፣ ጃዊ፣ ታች አርማጭሆ፣ ጠገዴ፣ አድአርቃይ ፣ አበርገሌ

ረ. ምድብ ስድስት

መተማ ፣ ምዕ/አርማጭሆ ፣ አብደራፊከተማ አስተደደር ፣ አብራጃራ ከተማ አስተደደር ፣ዝቋላ ፣ ሰሃላ፣

2 የስራ ቦታ ምድብ ደረጃ ነጥብ አሰጣጥ

ሀ. በምድብ አንድ ለሰራበት አንድ አመት አገልግሎት የሚሰጠው ነጥብ 1.0 ይሆናል፡፡

ለ. በምድብ ሁለት ለሰራበት አንድ አመት አገልግሎት የሚሰጠው ነጥብ 1.1 ይሆናል፡፡

ሐ. በምድብ ሶስት ለሰራበት አንድ አመት አገልግሎት የሚሰጠው ነጥብ 1.2 ይሆናል፡፡

መ. በምድብ አራት ለሰራበት አንድ አመት አገልግሎት የሚሰጠው ነጥብ 1.3 ይሆናል፡፡

ሠ. በምድብ አምስት ለሰራበት አንድ አመት አገልግሎት የሚሰጠው ነጥብ 1.4 ይሆናል፡፡

ረ. በምድብ ስድስት ለሰራበት አንድ አመት አገልግሎት የሚሰጠው ነጥብ 1.5 ይሆናል፡፡

# ክፍል አራት

## ስለ ተግባርና ኃላፊነት

### አንቀጽ 16. የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ባለሙያዎች/ የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ዝውውርና ምደባ ፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

1. በክልል ደረጃ የየቢሮዎች ተግባርና ኃላፊነት፣

ሀ. በቢሮዎች የሚደረገው የዝውውር ምደባ የሚፈፀመው በክልሉ ቢሮ በኩል ይሆናል ፡፡

ለ. ከዞን/ሪጆፖሊታን ወደ ዞን/ሪጆፖሊታን መደበኛ ዝውውር ፎርም በማዘጋጀት የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ባለሙያዎች/የቀበሌጽ/ቤት ኃላፊዎች በተወሰነው የጊዜ ሴሌዳ መሰረት የዝውውር ፎርም ተሞልቶ እንዲመጣ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል ፡፡

ሐ. የሚያስፈልጋቸውን የሰው ኃይል በመጠንና በሙያ ዓይነት ከበጀት ጋር በማገናዘብ ለቢሮው እንዲያሳውቁ ክትትል በማድረግ መረጃዉ እንዲጠናቀር ያደርጋል ፡፡

መ. ዝውውሩ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳና የማወዳደሪያ መስፈርት መሠረት እንዲፈፀም ያደርጋል

ሠ. የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ባለሙያዎች/ ወይም የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች መደበኛ ዝውውርና ምደባ ይከታተላል ፤ ይደግፋል፤ ይቆጣጠራል ህግ በሚፈቅደው መሰረት የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል ፡፡

ሰ. ለየሴክተሩ የሚያስፈልገውን የሰው ሃይል በሙያ አይነትና መጠን በመተንተን ያቅዳል ፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር በመደበኛ ዝውውር እንዲሟላ ያደርጋል ፡፡

ሸ. ቢሮዎች የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ባለሙያዎች/ ወይም የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች በመደበኛ ዝውውር ወይም በምደባ ለመመደብ በቅድሚያ በፎርም ቁጥር 15 የተፈቀደና በጀት ያለው ክፍት የስራ መደብ መኖሩን የማረገገጥ ግዴታ አለበት ፡፡

ቀ. ዝዉዉሩን በክልል ቢሮ በሰ/ኃ/አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የሚከናወን ሲሆን ከዞን ዞን የተዛወሩ ሰራተኞችን ለተዛወሩበት የዞን መምሪያ በደብዳቤ ያሳውቃል፡፡

በ. በኮሚቴ የተሰራውን ዝውውር ህጋዊነቱን በማረጋገጥ ቢሮ ኃላፊ/ምክትል ኃላፊ/ ተወካይ ኃላፊያፀድቃል፡፡

ተ. የዝዉዉር ስራዉን የሚከታተሉ እና በኮሚቴነት አብረው የሚሰሩ የሚመለከታቸዉን ባለሙያዎች ይመድባል፡፡

3. በዞን/ሪጀፖሊታን ደረጃ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ባለሙያዎች/ የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የሚሰሩበት መምሪያዎች ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. ከዞን/ሪጀፖሊታን ቀበሌ ወደ ሌላ ዞን/ሪጀፖሊታን ቀበሌ ለመዛወር የሚፈልጉ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ባለሙያዎች/ወይም የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የዝውውር ፍላጎት በተሞላበት የአስተዳደር ዕርከን የተሞላውን እያንዳንዱን የመደበኛ ዝዉዉር ፎርም በ2 ኮፒ በተገቢ ሁኔታ ዝውውር ፈላጊው ከሚሰራበት የወረዳ ጽ/ቤት እንዲላክለት በማድረግ መደበኛ ዝዉዉሩን ለመፈፀም በሚያስችል መልኩ መረጃውን በማጠናከር 1ዱን ለየቢሮዎች እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

ለ. ከወረዳ/ከተማ አስተዳደር ቀበሌ ወደ ወረዳ/ከተማ አስተዳደር ቀበሌ ዝዉዉር ፎርም በተገቢ ሁኔታ በወቅቱ ዝውውር ፈላጊው ከሚሰራበት የወረዳ ጽ/ቤት እንዲላክለት በማድረግ መደበኛ ዝዉዉሩን ለመፈፀም በሚያስችል መልኩ መረጃውን በማጠናከር ለዞን/ሪጀፖሊታን ሲቪል ሰርቪስ መምሪያ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

ሐ. የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ባለሙያዎች/ ወይም የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች መደበኛ ዝዉዉር በተቀመጠዉ የጊዜ ሰሌዳ ተግባራዊ እንዲሆን የውድድር መስፈርቱን መሰረት በማድረግ ለዞን /ሪጀፖሊታን ሲቪል ሰርቪስ መምሪያ እና ለወረዳ/ከ/አስተዳደር የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ባለሙያዎች/ ወይም የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የሚሰሩበት ጽ/ቤት ቴክኒካል ድጋፍና ክትትል ያደርጋል ፡፡ ችግሮች ሲያጋጥሙም አፋጣኝ መፍትሄ ይሰጣል፡፡

መ. በዝውውሩን ሂደት ይሳተፋል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፡፡

ሠ. ለዞን/ሪጀፖሊታን እና በስሩ ባሉ ወረዳዎች/ከተማ አስተዳደሮች የባለሙያ ፍላጎታቸውን መሰረት በማድረግ በመደበኛ ዝውውሩ እንዲሞሉ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ረ. የዝዉዉር ስራዉን የሚከታተሉ እና በኮሚቴነት አብረው የሚሰሩ የሚመለከታቸዉን ባለሙያዎች ይመድባል፡፡

ሰ. በኮሚቴ የተሰራውን ዝውውር ህጋዊነቱን በማረጋገጥ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ባለሙያዎች/ወይም የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የሚሰሩበት መምሪያ ኃላፊ/ምክትል ኃላፊ/ ተወካይ ኃላፊ ያፀድቃል ፡፡

4. በወረዳ/ ከተማ አስተዳደር ደረጃ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ባለሙያዎች/ የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የሚሰሩበትጽ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት፡-

ሀ. ከዞን/ሪጆፖሊታን ቀበሌ ወደ ሌላ ዞን/ ሪጆፖሊታን ቀበሌ እና ከወረዳ /ከ/አስተዳደር ቀበሌ ወደ ወረዳ /ከ/አስተዳደር ቀበሌ ለመዛወር የሚፈልጉ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች / ባለሙያዎች/ የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የዝውውር ፍላጎት በተሞላበት የአስተዳደር ዕርከን የተሞላውን እያንዳንዱን የመደበኛ ዝዉዉር ፎርም በ3 ኮፒ በተገቢ ሁኔታ ተደራጅቶ ከወረዳ ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት የተሰጠውን የዝውውር መረጃ 2ቱን ለዞን/ሪጆፖሊታን የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ ባለሙያዎች/ የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የሚሰሩበት መምሪያዎች እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

ለ. በወረዳው/በከተማ አስተዳደሩ ባሉ ቀበሌዎች የሚሰሩ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች /ባለሙያዎች/ የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የዝዉዉር ፎርም በወቅቱ አስሞልቶ ለወረዳው/ለከተማ አስተዳደሩ ሲቭል ሰርቪስ ጽ/ቤት ይልካል፡፡

ሐ. መደበኛ ዝዉዉሩ በተቀመጠዉ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እንዲፈፀም ድጋፍና ክትትል ያደርጋል ፡፡ ዝውውሩ በሚሰራበት ወቅት ቴክኒካል ችግሮች ሲያጋጥም አፋጣኝ መፍትሄ ይሰጣል፡፡

መ. በኮሚቴ የተሰራውን ዝውውር ህጋዊነቱን በማረጋገጥ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች /ባለሙያዎች ወይም የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ለሚሰሩበት ጽ/ቤት ኃላፊ/ምክትል ኃላፊ/ ተወካይ ኃላፊ ያፀድቃል ፡፡

ሠ. የዝዉዉር ስራዉን የሚከታተሉ እና በኮሚቴነት አብረው የሚሰሩ የሚመለከታቸዉን ባለሙያዎች ይመድባል ፡፡

5. የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ተግባርና ሃላፊነት፡-

ሀ. በቀበሌው ዉስጥ የሚሰሩ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች / ባለሙያዎች/ የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የዝውውር ፍላጎት በተሞላበት የአስተዳደር ዕርከን የተሞላውን እያንዳንዱን የዝዉዉር ፎርም በ4 ኮፒ በጥንቃቄ በማስሞላት በተወሰነዉ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት 3ቱንኮፒ በወቅቱ ለወረዳ/ለከተማ አስተዳደሩ ዝውር ፈላጊው ለሚሰራበት ጽ/ቤት እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

ለ. ለተቋሙ የሚያስፈልገዉን የሰዉ ኃይል በመጠንና በሙያ ዓይነት በመለየት በተቀመጠዉ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ለወረዳ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች / ባለሙያዎች/ወይም የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ለሚሰሩበት ጽ/ቤት እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

5 የዞን/ሬጆፖሊታን ሲቪል ሰርቪስና የሰ/ሀ/ልማት መምሪያ ተግባርና ኃላፊነት፡-

ሀ. ከዞኑ/ሬጆፖሊታን ቀበሌ ወደ ወረዳ/ከተማ አስተዳደር/ ቀበሌ ወይም ከወረዳ/ከተማ አስተዳደር/ ቀበሌዎች ወደ ሌላ ወረዳዎች/ከተማ አስተዳደሮች/ ቀበሌ ለመዛወር የሚፈልጉ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች / ባለሙያዎች/ የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የሞሉትን የተጠቃለለ የዝውውር ፎርም ዝውውር ፈላጊው የሚሰራበት መምሪያ በወቅቱ እንዲላክለት በማድረግ ዝውውሩን ለመፈጸም በሚያስችል መልኩ መረጃውን አደራጅቶ ይይዛል ፡፡

ለ. በተቀመጠው የማወዳደሪያ መስፈረት መሰረት በመደበኛ ዝውውር ከዞኑ/ሬጆፖሊታን ወደ ሌላ ዞን/ሬጆፖሊታን፣ከወረዳ/ከተማ አስተዳደር/ ቀበሌ ወደ ሌላ ወረዳ/ከተማ አስተዳደር/ ቀበሌ በኮሚቴነት ይሰራል፣ የኮሚቴውን የዝውውር ውጤት ከፀደቀ በኋላ ይፋ ያደርጋል፡፡

ሐ. የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች / ባለሙያዎች/ወይም የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የሚሰሩበት ቢሮ ከዞን/ሬጆፖሊታን ሲቪል ሰርቪስ መምሪያ የሚፈልገው መረጃ ሲኖር መረጃውን ይልካል፡፡

መ. በዞን ውስጥ የሚፈጸመውን የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ ባለሙያዎች/ወይም የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የዝውውርና ምደባ መመሪያ መተግበሩን ይከታተልል ይቆጣጠራል ፡

ሠ. የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ ባለሙያዎች/ ወይም የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች በሚሰሩበት ቢሮ አማካኝነት መደበኛ ዝውውር ከዞን/ሬጆፖሊታን ወደ ሌላ ከዞን/ሬጆፖሊታን ዝውውር የተሰራላቸው የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች / ባለሙያዎች ወይም የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች መረጃ ከዞን/ሬጆፖሊታን የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች / ባለሙያዎች/ ወይም የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የሚሰሩበት

መምሪያ በመቀበል ከወረዳ/ከተማ አስተዳደር/ ወደ ወረዳ/ከተማ አስተዳደር/ ከሚዛወሩ ባለሙያዎች ጋር እኩል እንዲወዳደሩ ይደረጋል፡፡

ረ. በክልሉ ቢሮ አማካኝነት መደበኛ ዝውውር የተሰራላቸው የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ባለሙያዎች/ወይም የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች መረጃ ከዞን/ሪጆፖሊታን የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ ባለሙያዎች/ወይም የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የሚሰሩበት መምሪያ በመቀበል ቢሮው ወደ ወረዳ/ከተማ አስተዳደር ለተመደቡ ባለሙያዎች ለተመደቡበት ወረዳ/ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት የምደባ ደብዳቤ ይልካል፡ ፡

6. የወረዳ/ከተማ አስተዳደር ሲቨል ሰርቪስና የስ/ሀ/ልማትጽ/ቤትተግባርና ኃላፊነት፡-

ሀ. በወረዳ/ከተማ አስተዳደር ቀበሌ የሚሰሩ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች / ባለሙያዎች/ ወይም የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የዝዉዉር ፎርም በወቅቱ በተገቢ ሁኔታ ተሞልቶ እንዲላክለት በማድረግ ዝውውሩን ለመፈጸም በሚያስችል መልኩ መረጃው እንዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡

ለ. ዝውውር ፈላጊው ከሚሰራበት የወረዳ ጽ/ቤት ተጠቃሎ የመጣለትን የመደበኛ ዝውውር መረጃ ትክክል ስለመሆኑ ከሰራተኛው የግል ማህደር ጋር ማረጋገጥ፡፡ የተሞላው መረጃ ስህተት ካለበት ከወረዳው ጽ/ቤት ጋር በመተባበር መፍትሄ ይሰጣል፡፡ የተስተካከለ መረጃ ለዝውውር ፈላጊ ባለሙያዎች ዕውቅና መፍጠር እና ቅሬታ ያለው ባለሙያ ካለ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ በማስተካከል ለዞን ሲ/ሰ/መምሪያ እንዲተላፍ ዝውውር ፈላጊው ላለበት የወረዳ ጽ/ቤት ያስላልፋል፡፡

ሐ. የሰራተኛውን የግል ማህደር በማየት የሰራተኛውን ስራ አፈፃፀም ውጤት በመሙላት እና የማህደር ጥራት ሁኔታ በማረጋገጥ ውጤት በመሙላት መረጃ ይሰጣል፡

መ. በተቀመጠው የማወዳደሪያ መስፈርት መሰረት በመደበኛ ዝውውር ጊዜ የዝውውር ፎርም የሞሉ በወረዳ ቀበሌ ያሉ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች / ባለሙያዎች/ ወይም የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ከሌላ ዞን/ሪጆፖሊታን ወይም ከወረዳ/ከተማ አስተዳደር ወደ ወረዳው/ከተማ አስተዳደሩ ተዛውረው የመጡ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች /ባለሙያዎች/ወይም የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎችን በማካተት በወረዳ/ከተማ አስተዳደር ደረጃ በኮሚቴነት ይሰራል፤ በኮሚቴ የተሰራውን የዝውውር ውጤት ከፀደቀ በኋላ ይፋ ያደርጋል፡፡

ሠ. የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች / ባለሙያዎች/ የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊዎችን የዝውውር መረጃ ይይዛል፣ አዲስ ምሩቅና በተለያየ ምክንያት ምደባ ለሚሰጣቸው ባለሙያዎችን ከየጽ/ቤቱ ጋር በመነጋገር በጀት ባለው ክፍት ቦታ ላይ ጊዚያዊ ምደባ ይሰጣል፡፡

## አንቀፅ 17. የዝዉዉር ኮሚቴ

1.የክልል የዝዉዉር ኮሚቴ/በየቢሮው ወይም በየተጠሪ ተቋማት የሚቋቋም ሆኖ

- የሰዉ ሀብት አስተዳደር ዳይሬክተር....ሰብሳቢ
- የኤክስቴንሽን ኮምኒኬሽን ዳይሬክተር /ተወካይ .....አባል /ለግብርና ቢሮ /
- የገጠር መሬት አስተዳደር ዳይሬክተር -----አባል/ለመሬት ቢሮ/
- የህብረት ስራ ማስፋፊያ ዳይሬክተር-------አባል /ለህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ባለስልጣን
- የሰዉ ሀብት አስተዳደር 2 ባለሙያዎች.....አባል
- ከቢሮው የሚመለከታቸው 3 ባለሙያዎች------አባል ይሆናሉ፣ ሆኖም ፀሀፊ በኮሚቴው የሚሰየም ይሆናል፡፡

2.የዞንና የወረዳ ዝዉዉር ኮሚቴ፡-

- የሰዉ ሀብት አስተዳደር ቡድን ቡድን መሪ....ሰብሳቢ
- የኤክስቴንሽን ኮምኒኬሽን ቡድን መሪ/ተወካይ .....አባል
- የገጠር መሬት አስተዳደር ቡድን መሪ -----አባል /ለመሬት ጽ/ቤት ወይም መምሪያ
- የህብረት ስራ ማስፋፊያ ቡድን መሪ----------አባል /ለህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት ወይም መምሪያ
- የሰዉ ሀብት አስተዳደር 2 ባለሙያዎች.....አባል
- በየመምሪያዎች ወይም በየወረዳው የሚመለከታቸው 3 ባለሙያዎች-------አባል

## አንቀጽ 18. ለዝውውር ክፍት ቦታዎችን ማሳወቂያና የዝውውር ወቅትና አፈጻጸም

### ሀ. ለዝውውር ክፍት ቦታዎችን ማሳወቂያ

1. ዝውውር ፈላጊው የሚሰራበት የወረዳ ጽ/ቤት ወረዳዎች በስራቸው ያሉ ክፍት ቀበሌዎችን በመለየት ከሀምሌ 5-10 ድረስ ለዞን ያሳውቃሉ

2. በዞኖች በስራቸው ባሉ ወረዳዎች የተላከውን ክፍት ቀበሌዎች በማጠቃለል ከሀምሌ 11- 16 ድረስ ለክልል ቢሮች ያሳውቃል

3. የክልል ቢሮዎች ከየዞኖቹ የተላከውን ክፍት ቀበሌዎች መረጃ በማጠቃለል ከሀምሌ 17- 25 ድረስ ለዞኖች ያሳውቃል

4. ዞኖች ከክልል ተጠቃሎ የመጣውን ክፍት ቀበሌ መረጃ ለየወረዳዎች ከሀምሌ 26-30 ድረስ ማሳወቅ

5. ወረዳዎች በክልሉ ያሉትን ክፍት ቀበሌዎች በየሙያ ዓይነቱ ሁሉም የቀበሌ ግብርና ልማት ባለሙያዎች እንዲያውቁት የሚደረግበት ጊዜ ከነሃሴ 1-5 ድረስ ማሳወቅ፡፡

### ለ. የዝውውር ወቅትና አፈጻጸም

1. ከቀበሌ ቀበሌ የሚሰራው ዝውውር በክፍት ቀበሌዎች ብቻ 2 አመት የሞላቸው ብቻ በየአመቱ እየተወዳደሩ ይዛወራሉ ፣ የወረዳ ወረዳ እና የዞን ዞን ዝውውር ደግሞ በሁለት አመት አንዴ እና ስር ነቀል ደግሞ በ5 አመት አንዴ የሚፈጸም ይሆናል፡፡
2. በሁሉም የዝውውር እርከን ደረጃዎች ከቀበሌ ቀበሌ፣ ከወረዳ ወረዳና ከዞን ዞን የዝውውር ፎርም በቀበሌ ደረጃ ተሞልቶ
   - ዝውውር ፈላጊው ለሚሰራበት የወረዳ ጽ/ቤት የሚደርስበት ከነሀሴ 6 እስከ ነሀሴ 10 ፣
   - ወረዳ ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት የሚደርስበት ጊዜ ከነሀሴ 11 እስከ ነሀሴ 12 ድረስ ሆኖ
   - ወረዳ ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት የዝውውር ፈላጊው ማህደር በማየት መረጃ የሚያጠቃልልበት ጊዜ ከነሀሴ 13 እስከ ነሀሴ 17 ይሆናል፣
   - የተጠቃለለው መረጃ በማስታወቂያ ሰሌዳ የሚለጠፍበት ጊዜ ከነሀሴ 18 እስከ ነሀሴ 20 ይሆናል ፣

➢ ማስተካከያ የሚያስፈልጉ ጉዳዮች ለማስተካከል ከነሀሴ 21 እስከ ነሀሴ 22፣

➢ ከወረዳ ወደ ዝውውር ፈላጊው ለሚሰራበት ዞን መምሪያ የሚላክበት ከነሀሴ 23 እስከ ነሃሴ 25

➢ ዝውውር ፈላጊው ከሚሰራበት ዞን መምሪያ ወደ ክልል ቢሮ የሰዉ ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የሚደርስበት ከነሃሴ 25 እስከ 30 ባሉት ቀናት

➢ ከነሃሴ 30 እስከ መስከረም 5 ደግሞ የመረጃ መጠናቀሪያ ጊዜ ይሆናል፡፡

3. በክልል ደረጃ ከዞን ዞን ዝውውር የሚሰራበት ጊዜ ከመስከረም 5 እስከ10፣ በዞን ደረጃ ከወረዳ ወረዳ ዝውውር የሚሰራበት ጊዜ ከመስከረም 10 እስከ 15 እንዲሁም በወረዳ ደረጃ ከቀበሌ ቀበሌ ዝውውር የሚሰራበት ጊዜ ከመስከረም15 እስከ 25 ባለዉ ጊዜ ዉስጥ ሆኖ ከመስከረም 25-መስከረም 30 የርክክብ ጊዜ ይሆንና ጥቅምት 1 ሁሉም በየተመደበበት ሙሉ በሙሉ ስራ የሚጀምርበት ነው፡፡

4. አንድ ዝውውር ጠያቂ ዝውውር ተሰርቶ ከማለቁ በፊት የዝውውር ጥያቄውን ከነሀሴ 24 በፊት መሰረዝ ይችላል፡፡

5. ሲቪል ሰርቪስና የሰ/ሀብት ልማት ኮሚሽን ሳይፈቅድ በዚህ የዝውውር መመሪያ ከተቀመጠው የዝውውር መስሪያ ጊዜ ውጭ የተከናወነ መደበኛ ዝውውር በህግ ተቀባይነት የለውም፡፡

6. ከአንድ ወረዳ ወደ ሌላ ወረዳ እና ከዞን ወደ ዞን በመደበኛው የግብርና ልማት ሰራተኞች፤ ባለሙያዎችና ጽ/ቤት ኃላፊዎች ዝዉዉር ከተሰራ በኋላ ወደ ተዛወረበት ቦታ ለመሄድ ፈቃደኛ ባይሆን በራሱ ፈቃድ ስራ እንደለቀቀ ይቆጠራል፡፡

7. የዝውውር መረጃ የሚላክበት ወይም የሚሰራበት ቀን ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም የበዓላት ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን እንዲሰራ ይደረጋል ፡፡

## ክፍል አምስት

## አንቀጽ 19. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

1. ለቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ባለሙያዎች/ ወይም ጽ/ቤት ኃላፊዎች ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ስምሪት በማካሄድና በተቋሙ ስራ ላይ የሚፈለገዉን ዉጤት ለማምጣት በዚህ መመሪያ በተቀመጠዉ ማወዳደሪያ መስፈርት መሰረትመመሪያዉ ላይ የተገለፀዉ የዝዉዉር ኮሚቴ በ2013 ዓ.ም የተሰራዉን ስርነቀል ዝዉዉር እንደ መነሻ አመት በመያዝ በየ5 ዓመቱ ስርነቀል ዝውውር እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡

2. በየደረጃው የተቋቋመውን ኮሚቴ በየደረጃው ባለው መ/ቤት የሚካሄደው መደበኛ ዝውውር የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

3. በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ሌሎች የዝውውር ጉዳዮች በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ 253/2010 እና ደንብ ቁጥር 75/2003 እና በምልመላ መረጣ መመሪያ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
4. በማንኛውም ደረጃ ዝውውር የተሰራለት የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኛ/ባለሙያ/ጽ/ቤት ኃላፊ በመንግስት እውቅና በመደበኛ ትምህርት፣ በክረምት ተከታታይ ትምህርት /ኮርስ/ ወይም የርቀት ትምህርት ፐሮግራም ወይም ተመሣሣይ ስልጠና በመጀመራቸው ምክንያት ወደ ተዛወሩበት ቦታ እንዳይሄዱ ሊከለከሉ አይችሉም፡
5. ከላይ በአንቀጽ 19 ተ.ቁ 4 የተለገፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በሥልጠና ላይ ያሉ የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ባለሙያዎች/ወይም ጽ/ቤት ኃላፊዎች ወደ ተዛወሩበት ቀበሌ፣ ወረዳና ዞን በሥልጠና ላይ መሆናቸውና ውል የገቡበትን ሠነድ ወይም ሥልጠናውን ያጠናቀቁ ከሆነም በገቡት የሥልጠና መመሪያ ውል መሠረት ምን ያህል ጊዜ እንደቀራቸው በክሊራንሳቸው ላይ ሊገለጽ ይገባል፡፡
6. የበጀት ዓመቱ ከመጠናቀቁ ከሁለት ወር በፊት የቀበሌ ግብርና ሰራተኞች/ ባለሙያዎች/ ጽ/ቤት ሀላፊዎች ክፍት የስራ መደብ ላይ የሰዉ ሀብት ስምሪት ማካሄድ አይቻልም፡፡
7. ዝርዝር የዝውውር መረጃ የደረሰው የቀበሌ ባለሙያ ዝርዝሩን አይቶ፣ የመረጃ መዛባት ተከስቶ ከሆነ መረጃው ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ በማመልከቻ የማስተካከያ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡ሆኖም ግን በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስተካከያ ጥያቄ ካልቀረበ የመረጃውን ትክክለኛነት እንዳመነበት ተቆጥሮ መረጃው ለዝውውር አገልግሎት ይውላል፡፡
8. የቅሬታ አቀራረብ

   በዚህ የዝዉዉር አተገባበር ላይ ቅሬታ ያለው የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኛ/ባለሙያ/ ጽ/ቤት ኃላፊ ቢኖር በመደበኛ ቅሬታ አቀራረብ ስነ ሥርዓት መሠረት የሚስተናገድ ይሆናል፡፡
9. በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ

   የሰው ሀብት አስተዳደርን በተመለከተ በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ አዳዲስ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በአዋጅ ቁጥር 253/2010 አንቀፅ 96 ን/አንቀፅ 2 በተናጠል አይቶ የመወሰን ስልጣን አለው፡፡
10. የተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

    ጥቅምት 10/2013 ዓ.ም ፀድቆ ሲሰራበት የነበረው የቀበሌ ግብርና ልማት ባለሙያዎች የዝውውር አፈጻጸም መመሪያና ይህን ተከትሎ በተለያዩ ጊዜያቶች የወጡ ሰርኩላሮችና ማብራሪያዎች በሙሉ በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡

11. ተጠያቂነት

ሀ. ለቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ባለሙያዎች/ወይም ጽ/ቤት ኃላፊዎች የዝውውር ቅጽ መሙያ ጊዜን የተቋማት ኃላፊዎች የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ባለሙያዎች/ወይም ጽ/ቤት ኃላፊዎች ሳያውቁት የዝውውር ጊዜው ቢያልፍባቸው በየደረጃው ያሉ ተቋማት ኃላፊዎች ወይም ተወካዮች ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

ለ. ማንኛውም የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኛ/ባለሙያ/ ወይም ጽ/ቤት ኃላፊ ሕጋዊ ባልሆነ ወይም በተጭበረበረ /የሐሰት/ ማስረጃ ጋብቻ እንደፈፀመ በማድረግ ወይም የሕክምና ማስረጃ ወይም በሌላ ምክንያት እንዲዛወር ያደረገ ወይም ያቀረበ መሆኑ ሲረጋገጥ እና ማስረጃ ሳያቀርብ እንደቀረበ አድርጎ ዝዉዉር የፈፀመ ወይም ያስፈፀመ በዲስፕሊን ስነ-ሥርዓት አፈጻጸም መመሪያ መሠረት ይጠየቃል፡፡ ሆኖም ጉዳዩ በሕግ የሚያስጠይቅ ሆኖ ከተገኘ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ይጠየቃል፡፡ የተፈፀመው ዝውውርም ይሰረዛል፡፡

ሐ. ይህን የዝውውር መመሪያ በተዛባ መልኩ ወይም ያለአግባብ የሚፈጽም የሚያስፈጽም አካል ወይም ኃላፊ አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

መ. በየደረጃው ተሞልቶ ለሚመለከታቸው አካላት በሚላከው የቀበሌ ግብርና ልማት ሰራተኞች/ባለሙያዎች/ወይም ጽ/ቤት ኃላፊዎች የግል መረጃ ላይ አላግባብ ተሞልቶ ለሚፈፀመው ችግር መረጃውን የሞላው ባለሙያ ወይም ኃላፊ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

12. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ ከፀደቀበት 20/10/ 2016 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ ያለ መብት ወይም ግዴታ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ሀብት ልማት ቢሮ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

ወ/ሮ ባንች አምላክ ገ/ማርያም

የአብክመ ሲቪል ስርቪስና የሠ/ሀ/ልማት ኮሚሽን

ኮሚሽነር

ቅፅ-1

**በአንድ ወረዳ ከቀበሌ ቀበሌ ለሚደረግ ዝውውር የዝውውር መሙያ ቅጽ**

ቀበሌ ------------------------------

| ተ.ቁ | ስም ከነ አያት | ፆታ | የትምህርት ደረጃ | የሰለጠኑበት ሙያ | የቅጥር ዘመን ቀን/ወር/ዓ.ም | የሙያ ስያሜ ደረጃና ደመወዝ | አሁን ከለበት ቀበሌ የተመደበበት ቀን/ወር/ዓ.ም | የሰራተኛው አገልግሎት ቀን/ወር/ዓ.ም | የትዳር አጋር አገልግሎት ቀን/ወር/ዓ.ም | አማካይ አገልግሎት ቀን/ወር/ዓ.ም | ባለትዳር ከሆኑ የትዳር ጓደኞቻቸው የሚኖሩበት/ የሚሰሩበት | | ለመዛወር የሚፈልጉበት ቀበሌበቅደም ተከተል | | | አሁን ያሉበት ቀበሌ የተሰጠው ምድብ ደረጃ | የሞላው ሰራተኛ ፊርማ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | ወረዳ | መ/ቤት | 1 | 2 | 3 | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

ቅፁን ያስሞላው ባለሙያ ሙሉ ስም----------------------

የስራ ድርሻ----------------------

ቀን---------------------

ፊርማ------------------

ያፀደቀዉ ሃላፊ ስም-----------------

የስራ ድርሻ-----------------------

ቀን-----------------------------

ፊርማ---------------------------

ቅጽ-3

<u>በአንድ ዞን ከዞን ዞን የዝውውር መሙያ ቅጽ</u>

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | የትምህርት ደረጃ | የሰለጠኑበት ሙያ | የቅጥር ዘመን ቀን/ወር/ዓም | የሙያ ስያሜ ደረጃና ደመወዝ | የሰራተኛው አገልግሎት ቀን/ወር/ዓም | የትዳር አጋር አገልግሎት ቀን/ወር/ዓም | አማካይ አገልግሎት ቀን/ወር/ዓም | ባለትዳር ከሆኑ የትዳር ጓደኞቻቸው የሚኖሩበት/ የሚሰሩበት | | ባለሙያዉ የሚሰራበት ወረዳና የወረዳ ምድብ ደረጃ | ለመዛወር የሚፈልጉበት ዞን በቅደም ተከተል | | | የባለሙያው ስልክ ቁጥር | ዝውውሩን የሞላው ሰራተኛ ፊርማ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | ወረዳ | መ/ቤ | | 1 | 2 | 3 | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

ዝውውሩን ያስሞላው ባለሙያ ሙሉ ስም---------------------

የስራ ድርሻ-----------------------------------

ቀን----------------------

ፊርማ--------------------

ያፀደቀዉ ሃላፊ ስም ---------------

የስራ ድርሻ-------------------------

ቀን-----------------------------

ፊርማ----------------------------